ከነቦ ዉቃዉ ጥቅምት 29/2000

አልበርታ-ካናዳ

# “የማቱ-ሳላ ዕድሜ!

# ለፀጋዬ የብዕር አርጩሜ!”

## “ላቶ!” ዕበጥ-ፈንዳት እንጂ

## ለወያኔ-ልሰግድ፤አልልክም አማላጂ

**ደግሞ፤ዛሬማ**

**ተንጠለጠለ፤ከ”አሎንባኩት”! ! !**

**የለዘዘ፤”ዓደንሀቆሬ”. . .**

**. . .አንዴም ሳያቅማማ**

**የከሃዲ፤”ሐቴርሳታ”. . .**

**የድፍረቱ፤”ሐሞና”. . .**

**. . .በፍፁም፤”ሎሩሃማ”**

**ዳግም፤ውርደትን ሊሰራ. . .**

**ጠራ፤ተንጠራራ**

**. . .የ አዞ “ቦኪም፤ባማ”**

**ፍርዱ አለደረሰው ይሆን?. . .**

**የጭረቱ አፈላማ።**

**አይ ፀጋዬ!**

**አርጩሜህ የዋዛ ነው?**

**“አስተናግር-ቅጠል” አለው፤**

ከነቦ-ዉቃዉ

አንዴ ሾጥ! ብታደርገው፤

የሚጨበጥ፤አሳጣው፤

መዘመዘው፤ቆጠቆጠው፤

አጠናገረው፤አጮለው፤

አንቀጠቀጠው፤አራደው፤

አንደባለለው፤ካፈር-ዶለው፤

የስር-ግንዱን አናዘዘው፤

የሆዱን-ሁላ ዘረገፈው።

ዕድሜ ላንተ ነው፤ፀጋዬ ደብተራው

አንተ-ግርፌ ዮሐንስ. . .

ቅኔህ ያልተጠጣ፤. . .

ዕፁብ-ድንቅ፤ጥንስስ. . .

አሳን በብርብራ፤ነበር የማጠምደው

ፀጋዬ-መንጎልህ፤አንሳፎ አወጣው

ለሶስት-አስርተ ዓመት…

. . .በሆዱ የታባው

አምቆ፤ያኖረው

ብቅል ሁነህበት. . .

አቃረ፤አቀረሸው

ገዳይ ና አስገዳይ. . .

ጠቐሚ፤አስጠቐሚ. . .

ራቁቱን ቀረው

**የወንድሜን ገዳይ. . .**

**ከ እጄ ላይ ጣልከው**

**የልቡን ነገርከው፤**

**እንደኮረኮርከው፤**

**የለበጣ፤አሳቅከው።**

**ተ-ና-ዘ-ዘ፤አ-ና-ዘ-ዝ-ከ-ው**

**እንዲህ ብሎ ተረተረው**

**ያንን የነፃነት እርሾ. . .**

**ያንን መቅረዝ. . .**

**ያንን ቀንዲል. . .**

**ከጃጀለው ለያጣጥል. . .**

**ከሙትም ሙትቻ እንጂ. . .**

**የመንጎሉ ክርፋት፤ጥምባት!**

**. . .ህሊና የለው፤አቅል**

**ዐይኑን በጨው አጥቦ. . .**

**ሃፍረት፤ውርደት፤ይናዘዛል?**

**የ አሎቶ ብዕር ሲገነፍል**

**የነዳይነቱ ብሂል፤ይሄን ብሉአል**

**“. . .ያለ ራእይ ሲደናበር፤**መድረሻው ግድ ሳይለው**እንደወጣ ቀረ** የሚባለው፤**ጆሮ በጠፋበት፤በተበላበት ዘመን ተወልዶ**ትዳር ብሎ፤ጨኽት ስራውን ነግዶ. . .አርባ ሊሆነው አይደል?እሱም ይኸው ሰባ ምናምኑን ጭሩአል. . .”

ለካስ ዕውነት ኑሮአል!

ይዋል፤ይደር እንጂ. . .

የሰው ደም ያዞራል

ከገቡበት፤ጉደጉአድ. . .

ጎርጉሮ፤ሰርስሮ፤. . .

ፈልፍሎ ያወጣል።

“ያላዋቂ-ሳሚ፤ንፍጥ ያጥለቀልቃል”

ጨው ለራስህ ስትል ብትጣፍጥ ይሻላል!

. . .“ግርዘ-ዲያቢሎስ”

ካልታቀበ፤ከቅርሻቱ ሊመለስ

ማሕበረ-ባንዳ-ግብስብስ

በደንጊያ ላይ፤ዉሃ ማፍሰስ

ዉሃ-ቅዳ፤ዉሃ-መልስ።

ነህና የደርግ ባለሙአል!

ፋሺስት-ባንዳ፤የምትባል

ወይስ፤ዕምቡቃቅላ፤ደላላ?. . .

የወያኔ-ምልምል?ገፍላ

“በቡሃ-ላይ፤ቆረቆር”

የንፁሃን ደም-ልከፍት

ያቅበዘብዛል፤ለመደፋት

“እስመ-አልቦ፤ዉስተ-ለመሬት”።

አሎቶ ከናባቱ. . .

ሲያሸቃብጥ፤ሲያረጠርጥ

አገር በፋሺስት ሲናጥ

ደም፤እንደ ዥረት ሲንዠጠዠጥ

የጀግና ልጅ አባ-እምቢዮ!

ለ ዐርነት ሲሞዣረጥ

አሎቶ የታሪክ-ምስጥ

አሳፋሪ፤ቅብጥብጥ

“የፋሺስት፤የወያኔ”. . .

አብሪ-ጥይት፤ቁንጥንጥ

በሙሽራው ወንድሜ ደም. . .

ከጅሎት ነበር፤ሊያንሻጥጥ

ግና

ሲያደፍጥ፤ሲያስደፍጥ

በፀጋዬ፤የብዕር-ፍልጥ

ላንቃ-አናቱን፤ሲፈለጥ

አደረጋት፤ፍርጥ-ፍርጥርጥ

ባንድነት፤ዕድገቱ ነው. . .

ማሸራሞጥ፤መሸራሞጥ።

መልዕክት አንድ

የዚህን ዝቃጭ ፅሁፍ ዝርዝር "እያቴን-ምከሩት" በሚል ርዕስ በ (www.addisvoice.com) ያገኙታል "ብፄዔ-ወ-ብፄ-ተራድኦ" ፤

ለ አዘጋጁም፦ "ፍሬን ለመኪና ብቻ ስላልሆነ ያገኙትን በጭፍን ከመለጠፍዎ በፊት ቆም ብለው ደጋግመው ያንብቡት፤አቂአሞ ከሆነ መልካም። የሰሞኑ ዉሎዎ አላማርኝም።

ቁልፍ (ፍቺ)

ከ"አሎንባኩት"! ! !የለቅሶ ዛፍ፤ " ዓደንሀቆሬ". .በጩኸት የተገኘ ምንጭ፤" ሐቴርሳታ". .አገር ገዠው፤"

ሐሞና". ብዛት፤ "ሎሩሃማ"ምህረት የማይገባው፤" ቦኪም፤ማልቀሻ፤ ባማ"፤ከፍታ

ቸር ይግጠመን

ከነበ-ወቃወ